# አያዋጣችሁምና ይቅርባችሁ!
# መልስ ለፕሮፌሰር ጌታቸውና አቦ ተፈራ

**ከባይሳ ዋቅ – ወያ**

ሰላም ወንድሞቼ፣ የግዜር ሰላም ይብዛላችሁ።
ሰሞኑን የኦሮሚኛ ቋንቋን ተጨማሪ የፌዴራል መሥርያ ቋንቋ እንዲሆን የቀረበውን ሃሳብ በመቃወም ፕሮፌሰር ለጻፉት አስተያየት የሰጠሁትን መልስ መሰረት በማድረግ ሁለታችሁም ባንድ ላይ አጸፋውን ለመመለስ መሞከራችሁን ልብ ይሏል። በግልጽ ላስቀመጥኳቸው ጥያቄዎች አንዳችሁም መልስ ለመስጠት ባትችሉም ወይም ባትፈልጉም፣ በመሞከራችሁ ብቻ ይህንን አጭር ጽሁፍ በመላክ፣ በዚህና ተያያዥ በሆኑ አርዕስቶች ላይ፣ ለምሳሌ የኦሮሚኛን በላቲን መጻፍ በተመለከተ ይካሄዱ የነበሩትን የውይይቶች ፋይሎች ለዘላለም ለመዝጋት ወሰንኩ። ቅንነት በሌለበት ሁኔታ ቅን ውይይት ለማካሄድ መሞከር ጊዜን ከማጥፋት ባሻገር፣ የተለየ ውጤት እንደማያመጣ እየታወቀና ለኦሮሞ ህዝብና ለቋንቋው ዕድገት የተቀረቆሩ አስመስለው አንድን ጉዳይ ለሃያ ሰባት ዓመታት ሙሉ መልሶ መላልሶ ለመዳሰስ መሞከር ዕርባና – ቢስ ተልዕኮ ይመስለኛል።
ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነው ደግሞ ፕሮፌሰርና አቦ ተፈራ ላቀረብኳቸው በጣም ቀላልና ግልጽ የሆኑ ጥያቄዎች አሳማኝ መልስ ሰጥቶ ፋይሉን እንደመዝጋት፣ አጋጣሚውን ተጠቅመው ስለ ፌዴራሉ ክልላዊ አስተዳደርና ኦሮሚኛን በላቲን መጻፍ ስለሚያስከትለው "ጉዳት" ለማውራት መረጡ። ይህ ደግሞ ቅንነት አይመስለኝም። ደግነቱ ግን ችግሩ ያለው በኛ "ተማርን" በምንለው የአንጋፋው ትውልድ ርዝራዦች መካከል እንጂ፣ ከሰማንያ በመቶ በላይ የሚሆነውና ከፌዴራል ሥርዓት ሌላ የማያውቀው የኢትዮጵያ ህዝብማ ስለ ክልላዊ አስተዳደሩም ሆነ ስለ ቁቤ፣ ብሎም አሁን በቀረበው ኦሮሚኛን ተጨማሪ የፌዴራሉ የሥራ ቋንቋ የማድረጉን ጥያቄ በተመለከተ አንዳችም ቅሬታ እንደሌለው ማስተዋሉ ተስፋን ያለመልማል።

ለናንተ ለሁለቱ የቁቤ ደምበኞቼ ጠቀሜታ ሳይሆን፣ ምናልባት በየዋህነት የሚከተሏችሁ ወገኖቻችን ሊኖሩ ይችላሉ ከማለትና እነሱም በናንተ ውስን አስተሳሰብ ተመርተው ትክክል ያልሆነ አቋም እንዳይወስዱና ዕውን በማይሆን ተስፋ ልባቸው ከሚንጠለጠል፣ በተቃራኒው ግን እውነቱን እንዲያውቁ ከማሰብ አኳያ፣ ከዚህ በፊት ያስቀመጥኳቸውን ጥያቄዎችና ለመደምደምያ የሚሆን የግል አስተያየቴን ላንዴና ለመጨረሻ እንደሚከተለው ለማስቀመጥ ፈለግሁ።

ጥያቄዎቼ ባጭሩ የሚከተሉ ነበሩ፣

ሀ) የኦሮምኛ ተጨማሪ የፌዴራሉ የሥራ ቋንቋ ሆኖ ቢያገለግል፣ ብሎም ከዛሬው የበለጠ ብዙ ዜጋ ቢያውቀውና ቢጠቀምበት ጉዳቱ ምኑ ላይ ነው? የኦሮምኛን ቋንቋ ባለማወቅ ለሥራ ፍለጋም ሆነ ምርትን ለመሸጥ ገበያ ፍለጋ በሚደረገው ከሰሜን ወደ ደቡብ ፍልሰት ሂደት አኳያ፣ የዜጎች የተለያየ ያገሪቷን ቋንቋ ማወቅና መንግሥትም ይህንን ቢያመቻችላቸው የሚጎዳ ግለሰብ ወይም ህብረተሰብ አለ ወይ?
ለ) የኦሮሞ ሕዝብ በላቲን ፊደል መጠቀም ከጀመረ ሰላሳ ዓመት ሊሞላው ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ አንድም የፊደሉ ተጠቃሚ የኦሮሞ ተወላጅ "አልተስማማኝምና በሳባውያን ፊደል ይቀየርልኝ" ብሎ አልጠየቀም። ታዲያ ይህ ከአርባ ከመቶ በላይ የሆነው የኦሮሞ ሕዝብ እየተደሰተበት ያለውን ፊደል ለማን ብሎ ነው እንዲቀይር የሚጠየቀው? የቋንቋው ተጠቃሚ ያልሆነው አካልስ በሌላ ህዝብ የቋንቋ አጠቃቀም ጉዳይ ውስጥ ገብቶ "የኔ የተውሶ ፊደል ካንተ የተውሶ ፊደል የተሻለ ነውና የራስህን ትተህ የኔን ተጠቀም" ብሎ ሙግት መግጠምስ ጤነኛ አስተሳሰብ ነው ወይ?

ሐ) የኦሮሞ ሕዝብ በላቲን ፊደል በመጠቀሙ በኢትዮጵያ የግዛት አንድነትም ሆነ በሕዝቦቿ ተከባብሮ አብሮ በእኩልነት በመኖር ላይ ያሳደረው ጫና ወይም ያስከተለው ጉዳት ምንድነው?

ጥያቄዎቼ ግልጽና ቀጥተኛ ነበሩ። በቅንነት መመለስ ለፈለገ ሰው መልሱ ከሶስት መስመር አይዘልም ነበር። ዕውኔታው ይህ ሆኖ እያለ፣

እንደው በደፈናው ወደማያስፈልግ አርዕስት ውስጥ እየገቡ፣ የሳባውያን ቋንቋ አገር-በቀል ይመስል፣ “የራሳችንን ፊደል ትተው ከባህር ማዶ ተውሰው” ወዘተ ማለቱ፣ የውይይቱን አቅጣጫ ለመቀየር ከመሞከር ሌላ አንዳችም ፋይዳ አይኖረውም። ይባስ ብሎ ደግሞ፣ ለረጅም ጊዜ “በሰፊዎቹ” ስንወነጀልበት የነበረው መሰረተ-ቢስ “የጠባብነት” ክስ ዛሬም ከግማሽ ምዕተ ዓመት በኋላ “ምሁሮቻችን” መልሰው መላልሰው እሱኑ ሲያኘኩ ማየቱ፣ ወይ ዋናውን ጥያቄ ለመመለስ ካለመቻል የመጣ ነው፣ አለያም የራስን ጠባብነት ለመሸፈን የተወጠነ ሴራ ይመስለኛል።



እስቲ ፕሮፌሰርና አቦ ተፈራ ካሉት አንድ ጭብጥ ላውጣና ማን ጠባብ ማን ደግሞ ሰፊ እንደሆነ ለኅሊና ፍርድ ላቅርብ። ኦሮሞዎች የሚሉት ወደ 50 በመቶ የሚጠጋው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚነጋገርበትን ኦሮምኛ ቋንቋን ከአማርኛ በተጨማሪ የፌዴራሉ የመስርያ ቋንቋ ይሁን ነው። ልብ በሉ፣ ከአማርኛ በተጨማሪ እንጂ በአማርኛ ምትክ አላሉም። በኦሮሞዎች ግምት፣ ኦሮምኛ ተጨማሪ የፌዴራሉ የመስርያ ቋንቋ ቢሆን፣ ያገሪቷን ምርት፣ የምርቶችና የሥራ ገበያ በማቅረብ ቀዳሚ በሆነው በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ያላንዳች ችግር ለመኖርና ለመስራት ያስችላል፣ ብሎም በህዝቦች መካከል መቀራረብንና መግባባትን ያጎለብታል ይላሉ። በኔ ግምት ይህ ነገሮችን አስፍቶ ከማየት የመጣና ሁሉንም የሚጠቅም፣ ማንንም ግን የማይጎዳ አግባብ ያለው ጥያቄ ነው። ፕሮፌሰርና አቦ ተፈራ ግን፣ አማርኛ ቀድሞ ቦታውን ስለያዘ፣ ኦሮምኛን ተጨማሪ የፌዴራል የሥራ ቋንቋ ማድረግ ጊዜና ሃብት ማባከን ስለሆነ አያስፈልግም ባይ ናቸው። በሌላ አነጋገር፣ ከአማርኛ ሌላ አንድም የኢትዮጵያ ብሄር ቋንቋ የፌዴራሉ የመሥርያ ቋንቋ ለመሆን ብቃት የለውም ባይ ናቸው። ከዚህ ባሻገር ግን ላገሪቷ የግዛት አንድነትም ሆነ የህዝቦች አብሮነት ላይ የሚያመጣውን አንድ እንኳ አሉታዊ ገጽታ ለአብነት ሊያቀርቡ አልቻሉም። በኔ ግምት ይህ “የእኔን አማርኛ ብቻ ተጠቀሙ” ማለት ነገሮችን አጥብቦ ከማየት የመጣና ማንንም የማይጠቅም፣ ሁሉንም ግን የሚጎዳ ውስን አስተሳሰብ ይመስለኛል።

እስቲ የቁቤ “ደምበኞቼን” አንድ ነገር ልጠይቃችሁ። ኦሮሚኛ ቋንቋን በላቲን ፊደል ለመጻፍ ላንድ ጊዜም እንኳ ቢሆን ሞክራችሁ ታውቃላችሁ ወይ? ሞክራችሁ ከሆነስ፣ በፊደሉ አጠቃቀም ላይ የከበዳችሁና ብሎም ለኦሮሚኛ ቋንቋ ዕድገት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል ብላችሁ የገመገማችሁት ነገር አለ? ካለ በአደባባይ አውጡና እንወያይበት። ይቅርታ አርጉልኝና እንደው ሳስበው፣ በተውሶ ላቲን ፊደል የሚጻፈውን እንግሊዝኛ ቋንቋን እየተማራችሁና ልጆቻችሁንም እያስተማራችሁ ምንም ቅር የማይላችሁ ሰዎች፣ በተውሶ ላቲን ፊደል የሚጻፈውን ኦሮሚኛ ቋንቋን ስታዩ ደማችሁ የሚፈላው፣ ከኦሮሚኛ ቋንቋና ከኦሮሞ ህዝብ ጋር አንዳች ዓይነት ጥላቻ ያላችሁ ያስመስልባችኋልና በጥብቅ ብታስቡበት ጥሩ ይመስለኛል።

በተረፈ ግን ወዳጆቼ፣ ወደዳችሁም ጠላችሁ፣ ፈለጋችሁም አልፈለጋችሁ፣ ዝቅ ብዬ የማነሳቸው ዕውኔታዎች፣ በተፈጥሮ ሂደት ካልሆነ በስተቀር ማንም ሊቀይራቸው የማይችላቸው ነገሮች ናቸውና፣ እናንተ ስላልፈለጋችኋቸው ብቻ እንደ እንፋሎት ተንነው የሚጠፉ መስሎአችሁ በማያዋጣ ክርክር ጊዜያችሁን ከምታጠፉ፣ ሌላ አንገብጋቢና ያገሪቷን ህልውናና የህዝቦቿን አንድነት ብሎም ወደ እርስ በርስ ግጭት ሊያደርስ የሚችል አደጋ እያንዣበበብን ነውና ፍልሚያውን ወደዚያ እናዙር እላለሁ።

ልትቀይሯቸው አትችሉም ያልኳቸው ዕውኔታዎቹ የሚከተሉት ናቸው፣

ሀ) በኢትዮጵያችን የኤኮኖሚው እድገት ልቆ ሄዶ ለምሳሌ ባንድ የማምረቻ ተቋም ሥር ከተለያዩ ብሄሮች የተወጣጡ ሰርቶ አደሮች ባንድ ጣራ ሥር የሚሰሩበት ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ የፌዴራሉም ሥርዓት ሆነ ክልሎቹ እንዳሉ ይቆያሉ። ዘላለማዊ ሥርዓት የለምና ፌዴራሊዝምም ደግሞ አንድ ቀን ይሞት ይሆናል። እስከዚያው ድረስ ግን በዛሬው የኢትዮጵያ ሁኔታ በተለይም የብሄር ጥያቄን በተመለከተ፣ እስከነጉድለቱም ቢሆን፣ ከፌዴራሉ ሥርዓት ሌላ ተስማሚ ሥርዓት ስለሌለ፣ በተግባር ሊውል ለማይችል ሌላ ሥርዓትን ከመመኘት ተነስታችሁ “ክልሎችን ማፍረስ” ወዘተ እያላችሁ ወገንን ማሳሳት ትርፍ የለውምና አካሄዳችሁንና አስተሳሰባችሁን ብትቀይሩ ይሻላል ባይ ነኝ።

ለ) በወያኔ አገዛዝም ሆነ በድህረ-ወያኔ መንግሥትም ሥር፣ ኦሮሚኛ የፌዴራሉ ተጨማሪ የመስርያ ቋንቋ እንደሚሆን ቅንጣት ታህል

ጥርጣሬ የለኝም። ታሪክ ግን የራሱን ቦይ ተከትሎ ስለሚሄድ ከኛ ግምት ውጪ በሆነ ሂደት የፌዴራሉ ሥርዓት ተገርስሶ ወደ ሌላ ብሄሮችን ወደሚጨቁን ሥርዓት ልንመለስ የምንገደድበት ሁኔታም ሊፈጠር ይችላል። ያ ደግሞ ከተፈጥሮ ሂደት ውጪ የሆነና የማንመኘው ኢዲሞክራሲያዊ የሆነ ሥርዓት ስለሚሆን፣ እንኳን ኦሮሚኛን የፌዴራሉ ቋንቋ እንዳይሆን ማገድ ብቻ ሳይሆን ኦሮሞዎችም በቋንቋቸው እንዳይጠቀሙ ሊያደርግ የሚችል ሥርዓት ሊሆን ይችላልና ዛሬ ላይ ሆነን እሱን መዳሰስ አላስፈላጊ ነውና፣ ዛሬ በጃችን ባሉትና ማድረግ በምንችላቸው ነገሮች ላይ ማተኮሩ የዜግነት ግዴታችን ይመስለኛል።

ሐ) ፕሮፌሰርና አቦ ተፈራ ወደዱም ጠሉም፣ የኦሮሞን ህዝብ ካሁን በኋላ በላቲን ፊደል የመጠቀሙን መብት የሚገድብ ምድራዊ ኃይል ያለ አይመስለኝም። በሁለት መቶ ዓመት ጊዜ ውስጥ የሳባውያንን ፊደል ተጠቅመው ከመጽሃፍ ቅዱስ በስተቀር አንድ እንኳ የታሪክ ወይም ልብ ወለድ መጽሃፍ ለማሳተም ያልቻሉትን ያህል፣ ባለፈው ሃያ አምስት ዓመት ብቻ የላቲንን ፊደል ተጠቅመው በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩትን መጽህፍ በመጻፋቸውና ቋንቋቸውን በማሳደጋቸው የፊደሉን ጥቅም በቅጡ ተረድተዋልና በምንም ተዓምር በሌላ በተለይም በሳባውያን ፊደል አይቀይሩትም። ደጋግሜም እንዳልኩትና "እያወቁ እንዳላወቁ" ለሚሆኑ ሳይሆን በየዋህነት የኦሮሞን ህዝብ "በባዕድ ፊደል መጠቀም" እንደ ጉዳት ለሚመለከቱ ዜጎች ለማለት የምፈልገው፣ ሂደቱ ሊቀለበስ የማይችል ደረጃ ላይ ደርሷልና፣ ላትመልሱት ነገር "በምሁራኖቻችን" ውስን አስተሳሰብ ተመርታችሁ ላታሸንፉ ለትግል አትዘጋጁ እላለሁ። በቅርቡ አንድ ጸረ-ቁቤ የሆነ "ምሁር" በኢትዮ ፎረም ላይ እንዳሰፈረው



"የላቲን ጉዳይ ዕልባት ካላገኘና አሁኑኑ ላቲንን ካላሸቀነጠርን፣ ላቲኑ የግጭት መንስኤ መሆኑ አይቀሬ ነው" ዓይነት ድፍረት ለተላበሰ የጠባቦች ቅስቀሳ ጆሮአችሁን አትስጡ ማለቴ ነው። የኦሮሞ ሕዝብ "በራሴ ቋንቋ ለመጠቀም የሚስማማኝን ፊደል እኔ ነኝ የማውቀው" ሲል አንዳንድ "ምሁራን" ግን "የለም ተሳስታችኋል፣ የሚጠቅማችሁን እኛ ነን የምናውቅላችሁ" ከሚለው አባባላቸው ባሻገር ነገሮችን ሰፋ አድርጋችሁ ለማየት ሞክሩ ማለቴ ነው። በሌላ አነጋገር የእኛ ትውልድ ከፊውዳሉ ዘመን የወረስነው የህዝቦችንና የቋንቋዎችን እኩልነት ያለመቀበል ባህል አለንና በኛ "ምሁራን" ልፈፋ አትበከሉ ማለቴ ነው።

ለኦሮሞ ህዝብ ከራሱ የተሻለ ሊያውቅለት ወይም ሊያስብለት የሚችል ግለሰብም ሆነ ማህበረሰብ ሊኖር አይችልም። ስለሆነም፣ "ለቋንቋህ እድገት ይሽኛው ይሻላልና ያኛውን ተው" ብሎ ለመምከር መሞከር ትንሽ መስመር የዘለለና አላስፈላጊ የሆነ "ምክር" ይመስለኛል። በግሌ ለምሳሌ፣ ከደረሰብኝና ዛሬም በዲያስፖራ ያሉት ጓደኞቼ ልጆቻቸውን ከሁለት መቶ ሰባ በላይ ፊደላትን ባቀፈው የሳባውያን ፊደል መጻፍን እንዲማሩላቸው የሚያዩትን ፍዳ ሳስተውልና በአንጻሩ ደግሞ የኦሮሞ ልጆች ሃያ ስድስት ፊደላትን ብቻ ባቀፈው የላቲን ፊደል ኦሮሚኛን በትንሽ ጊዜ ውስጥ በቀላሉ ማንበብና መጻፍ መቻላቸውን ሳስብ፣ አማርኛም በላቲን ፊደል ቢጻፍ ኖሮ ለመማር መቅለሉን ብቻ ሳይሆን ለዘመናዊ ቴክኖሎጂም ተስማሚ ሆኖ ቋንቋውን በደንብ ለማሳደግ ይረዳል የሚል ግምት አለኝ። ግን ደግሞ፣ የአማርኛ ቋንቋ ባለቤት ባለመሆኔ በሰው ቋንቋ ገብቼ "ላቲን ይሻላችኋልና ሳባውያኑን ተውት" ብዬ ለመምከር ብሞክር አሳፋሪ ይመስለኛል። ይህ በራስ ባልሆነ ጉዳይ ገብቶ "እኔ ካንተ የተሻለ የሚጠቅምህን አውቅልሃለሁና የምልህን ተቀበል" ማለት ከፊውዳሉ ሥርዓት የወረስነው ኋላ ቀርና የቋንቋን ብቻ ሳይሆን የህዝቦችን እኩልነት አምኖ ካለመቀበል የመነጨ እኩይ ተግባር ይመስለኛል።

በፖሊቲካ ሂደት ውስጥ፣ ከሁሉም በላይ የሚያሳፍር ነገር ቢኖር፣ አንድን ፍልሚያ መጀመር ሳይሆን የማያሸንፉትን ፍልሚያ መጀመር ነው ይላሉ ፈረንጆች። እስቲ ወዳጆቼ አደብ ግዙና ላንዳፍታ እንኳ ቆም ብላችሁ እያደረጋችሁ ያላችሁትን ገምግሙ። ለሃያ ሰባት ዓመት ያላሰለሰ ጥረታችሁ ውስጥ ከዶክተር ፍቅሬ ቶሎሳ በስተቀር የአንድም ኦሮሞ ምሁር ድጋፍ ለማፍራት አለመቻላችሁን ስትገነዘቡ "ይህ የማይገባው የኦሮሞ ህዝብ አስበንለት የላቲንን ፊደል ትቶ በሳባውያን ፊደል እንዲጠቀም ከልብ የመነጨ ምሁራዊ ምክር ብንሰጠው አልገባ አለው" ብላችሁ "ምክሩን" ማቆም ነበረባችሁ። ትግላችሁ በቅንነት ለኦሮሞ ህዝብ በጎ ከማሰብ ተነስቶ ከሆነ፣ ስላሰባችሁልንና እስካሁን ድረስ ያለመታከት ላደረጋችሁት የማሳመን እንቅስቃሴ ከልባችን እናመስግናችኋለን፣ ግን ደግሞ ስለቋንቋችን አጠቃቀም ከኛ የተሻለ የሚያውቅልን ስለሌለ እሱን ለኛ ተውልንና ይልቅስ አማርኛ ቋንቋን በላቲን ፊደል ብንጽፍ ሊያመጣ ስለሚችለው ጥቅም "ምሁራዊ" ምርምር በማድረጉ ላይ አተኩሩ እላለሁ።

ለመደምደም ያህል፣ የኦሮሚኛ በላቲን ፊደል መጻፍ የሚያስከትክለው ጉዳት “ተሰምቷችሁና ለኦሮሞ ህዝብ በጎ ከማሰብ” እንቅልፍ ከምታጡ፣ በሌላ አገራዊ ጉዳይ ላይ ተስማምተን፣ ላቲን ፊደልን ሳይሆን፣ ይህን ግፈኛ የወያኔ መንግሥትን እንዴት አርገን አሽቀንጥረን ለመጣልና በምትኩ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት የምንመሰርትበትን ዘዴ በጋራ በመቀየሱ ላይ ብንረባረብ የተሻለ ይመስለኛል።
በሌላ ወቅታዊ አርዕስት ላይ ለመወያየት እስንገናኝ ድረስ በሰላም ሁኑ።

******

ጄኔቫ፣ 20 ማርች 2018 ዓ/ም
wakwoya2016@gmail com